የሰ/መ/ቁ 69125
ታህሣሥ 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሠላም ተስፋዬ ጠበቃ ዳንኤል ግርማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አልካን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሙሉጌታ ሀመነ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ ውል ከህግ ውጭ ያቋረጠ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች የተቀጠሩት በዲኘሎማ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር ነበር፡፡ በዲኘሎማ ኮርስ እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዳይሰጥ ከመንግሥት ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ ከሥራ የተሰናበቱ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በአዋጁ መሠረት የካሣና ሌሎች ክፍያዎች ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያለውን የሥራ ውል ያቋረጠው በህግ በተደነገገው መሠረት ነው በማለት ከወሰነ በኂላ ተጠሪ ለአመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተው በህጉ በተደነገገው መሠረት ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በመንግስት ትዕዛዝ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለዲኘሎማ ተማሪዎች እንዳይሰጥ መከልከሉና በዚህ ምክንያት ተጠሪ የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተጠሪን የማስጠንቀቂያ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም በማለት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ የሥራ መደቡን አልሠረዝኩም፡፡ የሥራ መደቡ ለዲኘሎማ ትምህርት እንደማያስፈልግ ትዕዛዝ የተሰጠው በመንግስት ነው፡፡ ስለዚህ በመንግስት ትዕዛዝ የሥራ መደቡ አላስፈላጊ የሆነ በመሆኑ የማስጠንቀቂያና የሥራ ስንብት ክፍያ የምከፍልበት ምክንያት የለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት የተቀጠሩት ድርጅቱ በዲኘሎማ ትምህርት ለሚያስተምራቸው ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር እንደነበር በፍሬ ጉዳይ ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ እያስተማሩ በነበሩበት ጊዜ መንግስት በዲኘሎማ ደረጃ ለሚሰጥ ትምህርት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መስጠት የሌለበት መሆኑን የሚገልፅ መመሪያ ማውጣቱ የሚያከራክር አይደለም፡፡

አመልካች የተቀጠሩበት የሥራ መደብ በዲኘሎማ ደረጃ ትምህርት ለሚሰጡ ተቋማት እንደማያስፈልግና አመልካች ያስተምሩት የነበረው ትምህርት ሊሰጥ እንደማይችል መንግስት መመሪያ ያወጣበት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው ከዚህ በኂላ በተቋሙ የሚሠሩት ሥራ የለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በራሱ አነሳሽነት አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው በህግ ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል በተላለፈው መመሪያ መሠረት አመልካች የሚያስተምሩት የእንግሊዝኛ ቋንቋ በዲኘሎማ ደረጃ መሰጠት የሌለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ አስገዳጅ ትዕዛዝ ስለደረሰው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከአቅሙ በላይ በሆነ ሁኔታ ሥልጣን ባለው አካል በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት በመሆኑ በጉዳዩ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያና የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ መሠረት ለአመልካች ተሠጥቷት የነበረው ሥራ ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል ባወጣው መመሪያ መሠረት አመልካች እየሠራች ለመቀጠል የማትችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚሰጠው ሥራ በሌለበት ሁኔታ የሥራ ውሉ እንዲቀጥል የማድረግ ህጋዊ ግዴታ የለበትም፡፡ የሥራ ውሉ በመንግስት በወጣ መመሪያ ተፈፃሚነት ምክንያት የተቋረጠ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያም ሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ